King County

# *የ2023 የግዛቱ ሕግ አውጪ*
# *የእድገት ውስንነት ላለባቸው ቅድሚያ የሚሰጡዋቸው*

*በኦክቶበር 27፥2022 ታድሷል*

የኪንግ ካዎንቲ ሕግ አውጪው የእድገት ዝግመት ወይም ውስንነት ላለባቸው ሕፃናት የእድግትና የአህምሮ ውስንነት ላለባቸው ግለሰቦች (I/DD)፥ እንደዚሁም ደግሞ ለቤተሰቦቻቸው ላደረጉት ቀጣይ ድጋፍ ያመሰግናል። የኪንግ ካዎንቲ ፀረ-ዘረኛ ካዎንቲ ለመሆን በማሰብ የሚያደርጋቸው ጥረቶች ስራውን አካል ጉዳተኝነት ባለባቸው ማህበረሰቦችና በጥቁር፣ በነባሮች፥ እና በቀለም ሰዎች ላይ ለማተኮር ያለውን ቁርጠኝነትን ያካትታል።

**ኪንግ ካዎንቲ የህግ አውጭው አካል በሀብት ተደራሽነትና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ፍትሃዊነትን ለማስቀጠል ቅድሚያ እንዲሰጥ የማህበረሰብ ድምጽን በማክበር በ2023 የሚከተሉትን እርምጃዎች እንዲወስድ ይጠይቃል፡**

1. ***በቋንቋ ተደራሽ የሆኑትንና ከባህል ጋር ተዛማጅነት ላላቸው አገልግሎቶች የገንዘብ ድጋፍን መጨመር።*** *ሁሉም* I/DD *ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው በቋንቋቸውና በባህላቸው አገልግሎቶችን እንዲያገኙ በቃላት ገለጻ፣ በትርጉም፣ በባህል አሰሳና በሌሎች የቋንቋ እንደዚሁም የባህል ድጋፎች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ።*

2. *የማህበረሰብ አባላት አገልግሎቶችን እንዲያገኙና የካዎንቲውን አስተዳደር ምጣኔን ለመጨመር የአቅራቢዎችን ኔትወርኮች ለማረጋጋት የዋጋ ጭማሪን የሚያጠቃልል* ***የዋሽንግተን ስቴት የማህበራዊና የጤና አገልግሎቶች መምሪያ የስራ ቅጥርና የቀን ተመን ጥናት ምክረ-ሐሳቦችን ፈንድ ያድርጉ።***

3. ***ዝግመትና የአካል ውስንነት ያለባቸው ታዳጊ ልጆች (0-5) ላላቸው ቤተሰቦች ጥራት ላላቸው ድጋፎችና አገልግሎቶች ተደራሽነትን ያሻሽሉ እንደዚሁም ደግሞ ለድጋፎች እንቅፋት የሚሆኑትን ያስወግዱ።*** *ለጨቅላ ህፃናትና ለታዳጊ ህፃናት ቅድመ ድጋፍ ቤተሰብ ከኪስ የሚያወጣቸው ወጪዎችን ማስወገድን ጨምሮ የልጆችና የቤተሰብ ፍላጎቶችን ለመደገፍ በስርአቶች ውስጥ የተቀናጁ ጥረቶች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ።*

4. ***ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሚወጡ ተማሪዎች የገንዘብ አገልግሎቶች።*** *በ*2023-2025 *ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለወጡ ብቁ ለሁኑ ተማሪዎች ከትምህርት ቤት ባሻገር የሚያደርጉትን ጉዞ ለመደገፍ ለሁሉም የስቴት የአካል እድገት ውስንነት ያለባቸው አስተዳደር መሰረታዊ የፕላስ ወይቨር አገልግሎት ያቅርቡ።*

5. ***ማህበረሰብን መሰረት ያደረጉ የቤት መፍትሄዎችን ለመደገፍ በአውስ ትራስት ፈንድና በሌሎች የገቢ ምንጮች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ።*** *እነዚህ ኢንቨስትመንቶች የ*I/DD *ውስንነቶች ያለባቸው ሰዎችና ቤተሰቦቻቸው ተደራሽ፣ ፍትሃዊ በሆነ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እንደዚሁም በተመጣጣኝ ዋጋ በአካባቢያቸው ማህበረሰብ ውስጥ መኖር እንዲችሉ ለማረጋገጥ ያስፈልጋል።*

6. **በI/DD *የባህሪ ጤና ድጋፎች ላይ ኢንቨስት ያድርጉ።  ግለሰቦችና ቤተሰቦች ያሉት የተለያዩ የባህርይ ጤና ድጋፎችን ይፈልጋሉ።*** *እያደገ ለመጣው የባህሪ ጤና ቀውስ የሚሰጠው ምላሽ* I/DD *በመረጃ የተደገፈ አጠቃላይና ከቤት ውጪ አገልግሎቶች በተጨማሪ ተደራሽ አማራጮችን ማካተት አለበት።*

*ለተጨማሪ መረጃ፥ እባክዎትን በዚህ ያግኙን፡*
*ሚሸል ዋይት* (Michael White)*፥ የኪንግ ካዎንቲ ጽ/ቤት አስተዳደር፥* michwhite@kingcounty.gov / 206-206-351-1674